በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብተና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ
**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**National Archives and Library Agency**

# የአንጋፋ አርቲስቶች መዝገበ የሕይወት ታሪክ
# Biographycal Bibliography of Senior Artists

**ቅፅ 25፣ቁጥር 4፣ 2000 ዓ.ም. Vol. 25, No.4, 2008**

በሕትመት ማግኛና ዩኒየን ካታሎግ መምሪያ
በናሽናል ቢብሊዮግራፊ ቡድን ተዘጋጀ

**Prepared by**
**Union Catalogue and Acquisition Department**
**(National Bibliography Team)**

**መጋቢት 2000**
**MARCH 2008**

# መ ግ ቢ ያ

ሙዚቃ በኢትዮጵያ ከተጀመረ አያሌ ዘመናት አልፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሠረተ ታሪክ ለማውሳት « ዳዊት በበገና እዝራ በመሰንቆ ያንቆረቆረሽ » የተሰኘውን ጥንታዊ የማሞካሻ አባባል መጥቀስ ያሻል፡፡ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጥንታውያን የቤተክህነት ሊቃውንት ጸሎታቸውን በሙዚቃ ያቀርቡ እንደነበር ይተረካል፡፡ ሊቁ ያሬድ ፍልስፍናውን በሙዚቃ ላይ መስርቷል፡፡ በጠቅላላው ሙዚቃ ለጸሎት፣ ለዘፈን፣ ለለቅሶና ለጦርነት ማወጃ ሲያገለግል የቆየ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሙዚቃ በሁለት ተከፍሏል፡፡ እነሱም ዘመናዊና ባሕላዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡ እረኛው በየሸንተረሩ፣ አረሆው በየመጠጥ ቤቱ እድምተኞች በየሰርጉ ቤት የሚያዜሙት ባሕላዊ ዘፈን ወዙን ሳያጣ ትዝታው ዛሬም በየቀበሌው እንደተንሰራፋ ይገኛል፡፡ በአንጻሩም ዘመናዊ ዜማዎችን እያቀናበሩ የሚያቀርቡ የሙዚቃ ክፍሎች ከየአቅጣጫው እንደ እንጉዳይ ብቅ ብቅ በማለት ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያን የሙዚቃ መንስኤና ግስጋሴ በዚህ አጭር መግለጫ ማቅረብ የሚያዳግት ቢሆንም በሃገሪቱ ውስጥ በባህላዊ ሙዚቃ ከፍተኛ ዝና የነበራቸውን እንደ እነ አዝማሪ ጻዲቋ (ሸጉጤ)፣ ባፈና! እና እነ አዝማሪ አቡኑ የተባሉትንና እንደ እነ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ የመሳሰሉት የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለመጀመሪያ ጊዜ በሸክላ በማስቀረጽ ለአውሮፖውያን ያሳወቁትና ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ዕድገት መሠረትና ፋና ወጊ የነበሩትን በሙዚቃው ዓለም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉትን አንጋፋ የሙዚቃ ባለሙያዎች ሥራዎቻቸው እና አስተዋጽኦቻው ተረስቶ እንዳይቀር ሲባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ በዚህ ዕትሙ ውስጥ የአንጋፋ ወንድ አርቲስቶችን ታሪክ ለትውልድ አቆይቶ ለማስተላለፍ ሲባል አጫጭር የሕይወት ታሪካቸውን አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

ለዚህ አገር አቀፍ ለሆነ ዓላማ የአርቲስቶችን የህይወት ታሪክ በተሟላ መልኩ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ማንኛውም የሚመለከታቸው አካላትም በሙዚቃው ዓለም በህይወት ዘመናቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ የነበሩትን አርቲስቶች ሥራዎቻቸው የትም ተረስተው እንዳይቀሩ እና እንዳይጠፉ የየበኩሉን እገዛ ሊያደርጉ ይገባቸዋል እንላለን፡፡

# የአርዕስት ማውጫ


| አርዕስት | ገፅ |
|---|---|
| *ሙዚቃ በኢትዮጵያ* | *4* |
| የሙዚቃ ትምህርት ቤት | 5 |
| የሸክላ ማጫወቻ (ግራማፎን) | 5 |
| የአርቲስቶች ዝርዝር ታሪክ | 6-32 |
| የኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች | 33 |
| የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች | 33 |
| የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች | 34-35 |
| የቃላት ማውጫ | 36 |

# ሙዚቃ በኢትዮጵያ

ግርማዊ ጃንሆይ በአልጋ ወራሽነታቸው በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. አውሮፖን ጎብኝተው ሲመለሱ አርባ የአርመን ተወላጆች በበጎ አድራጐት ለመርዳት ካስመጧቸው የመንፈስ ማነቃቂያና የሞራል መጠበቂያ እንዲሁም ለሀገሪቱ የሥልጣኔ እርምጃ ይጠቅማል በማለት የሙዚቃ ትምህርት ቤት አቋቋሙ:: ከዚህ በኋላ በዚሁ ዓመተ ምሕረት ከወለጋ ጠቅላይ ግዛት ከሾጐሌ ፲፰ የሚሆኑ ወጣቶች መጥተው በሙዚቃ ትምህርት እንዲሰለጥኑ ተደርጎ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. የግርማዊ ጃንሆይ ንግሥ በዓል በነዚሁ ሙዚቀኞች ተከብሮ ውሏል:: እነዚህ የመጀመሪያው ኢትዮጵያውያን ሙዚቀኞች በ፳ቱ የመከራ ጊዜ ግማሾቹ በጠላት ሲገደሉ የቀሩትም ተበታትነዋል::

የኢትዮጵያ ነፃነት እንደተመለሰ ይኸው የሙዚቃ ክፍል ድርጅት አስፈላጊ በመሆኑ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. መስከረም ፳፩ ቀን ጀምሮ እንደገና እንዲቋቋም በግርማዊ ጃንሆይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ከጠላት በፊት በቦይስካውትና በየትምህርት ቤቱ የሙዚቃ ትምህርት የጀመሩ ስለነበሩ ተመርጠው በካፒቴን ኬ.ናልባንዲያን አስተማሪነት ሥራው በክቡር ዘበኛ ድርጅት ውስጥ ተጀመረ::

በሀገራችን የሙዚቃ ሥለጣኔ የተስፋፋውና የተጀመረው ከውጭ ሀገር የሙዚቃ መምህራኖችን በማስመጣት በክቡር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ሲሆን ለዚሁ ክፍል ከሰለጠኑት ብዙዎቹ በልዩ ልዩ ድርጅቶች ውስጥ በመሰማራት የሀገራቸውን ወጣቶች በሙዚቃ ጥበብ በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ:: ከዚህም በተረፈ ድርጅቱ ያሰለጠናቸውን የሙዚቃ አዋቂዎች በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ወደ ምድር ጦር ሙዚቃ ክፍል እየላከ እንዲያስተምሩ አድርጓል ::

በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. የአ.አ. ማዘጋጃ ቤት አሁን የቀ.ኃ.ሥ.ቴአትር ክፍል የተባለው ተቋቁሞ ቲያትር በሚታይበት ጊዜ የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ረድቷል::

የክብር ዘበኛ ሙዚቀኛ ክፍል በግርማዊ ቀ.ኃ.ሥ. መልካም አሳቢነት ከ፲፱፲፯ ዓ.ም ሥራውን ከወጠነበት ቀን ጀምሮ የተጣለበትን አደራ በሚገባ ያከናወነ ለመሆኑ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ክፍሎች የረዳ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአማርኛ ሙዚቃን አራቆ በመቀመር ለሌሎች ሁሉ መልካም አርአያ ሆኖ የኢትዮጵያ ዜማ ከሀገሩ አልፎ በሌላው ዓለም እንዲታወቅ አድርጓል:: በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. በቀ.ኃ.ሥ.ቴአትር ቤት በተደረገው የሙዚቃ ውድድር የክ/ዘ ሙዚቃና ቲያትር ክፍል ፩ኛ ሆኖ የተሸለመ ከመሆኑም በላይ እስከ ዛሬ ድረስ ሌላ ውድድር ስላልተደረገ የከፍተኛነቱን ደረጃ አሁንም እንደያዘ ነው::

## *የሙዚቃ ትምህርት ቤት*

- *የሙዚቃ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ የተከፈተው በ1887 ዓ.ም ነው፡፡*
- *ምኒልክ ከሩሲያ የሙዚቃ አስተማሪ አስመጥተው ትምህርት ቤቱን በከፈቱበት ጊዜ ከመምህሩ ጋር 40 የተለያዩ ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያዎች መጥተው ነበር፡፡*
- *አሁን ያለው አንጋፋው የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ተመርቆ የተከፈተው ሰኔ 30 ቀን 1962 ዓ.ም.*

## *የሸክላ መጫወቻ /ግራማፎን/*

- የመጀመሪያውን ግራማፎን በ1889 ዓ.ም ሄንሪ ደ አርሲንስ እና ኒኮላስ ሊዋንቲቭ ለምኒልክ አመጡላቸው፡፡ ይኸውም መጫወት ብቻ እንጂ ድምጽ አልነበረም፡፡ በኋላ ግን በዓመቱ በ1890 ዓ.ም ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላኩ የእንግሊዝ መልእክተኞች በመጡ ጊዜ ግራማፎኑንና ድምፅ መቅጃውን ይዘውላቸው መጡ፡፡
- ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፃቸው በዲስክ የተቀረፀው የምኒልክና የጣይቱ ነው፡፡ ዛሬ በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ ብሪቲሽ ኢንስቲቲውት ኦፍ ሪኮርድ ሳውንድ በተባለው ሙዚየም ውስጥ ይገኛል፡፡

# የኢትዮጵያ ድምፃውያን ሁሉ ባለ ድምፅ »

## በሀገራችን የመጀመሪያው የዜማ ሸከላ

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ስልጣኔ ጅማሮን ስንመለከት ዳግማዊ አጤ ምኒልክን የስልጣኔ ፈር ቀዳጅ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ንጉሱ ሀገራቸውን ከአውሮፖ ስልጣኔ ጋር ለማስተዋወቅ የፀና ዓላማ ነበራቸው፡፡ በወቅቱ ከነበረው ልማድ፣ እምነትና ባህል ጋር ተፋልመው የዘመናዊ ኢትዮጵያን መሠረት ጥለው አልፈዋል፡፡



# ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ

በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ( Recording History ) በሸክላ የተቀረፀ የመጀመሪያው ዜማ የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ስራዎች ሲሆኑ ዘመኑም በአጤ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ነበር፡፡

ተሰማ እሸቴ የተላኩበትን የሹፌርነትና የመካኒክነት ትምህርት አጠናቀው አጥጋቢ ውጤት ከማምጣታቸውም በላይ የመጀመሪያውን የአማርኛ ዜማ ሸክላ እዚያው በጀርመን ሀገር ሆነው ለማስቀረፅ በቅተዋል፡፡ በጀርመን ቆይታቸው ወቅት የጀርመን የሙዚቃ ድርጅት ጠይቋቸው የኢትዮጵያ ***መዲናና ዘለሰኛ*** ዜማዎች በ17 አይነት ስልት እየተጫወቱ ተቀርፀዋል፡፡

ኩባንያው የተሰማ እሸቴን ዜማዎች በ17 ሸክላዎች የቀረፀው ሲሆን ለዜማው ባለቤት የድካም ዋጋ እንዲሆን በወቅቱ 17 ሺህ የጀርመን ማርክ ከፍሏቸዋል፡፡ በዘመኑ ብቻ ሳይሆን በሀገራችን አሁንም እነዚህ የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ብርቅዬ ሸክላዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ውስጥ ተሰብስበው ይገኛሉ፡፡

እነዚህ በተቋሙ እጅ ያሉት 16 ሸክላዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዜማዎችን የያዙ ሲሆኑ ባጠቃላይ 32 ዜማዎች ተቀርፀውባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ የሸክላው ገፅ  ላይ A ወይም B ተብሎ ተሰይሟል፣ የዜማው ስም ተፅፎበታል፤ የዜማው ባለቤት ተሰማ እሸቴ ስም አለ፤ ሸክላው ጀርመን ሀገር መሰራቱ እንዲሁም የሸክላው ቁጥር ተጠቅሷል፡፡

በ1925-26 ዓ.ም. አካባቢ የእነ ፈረደ ጐላ፣ ንጋቷ ከልካይና ተሻለ መንግሥቱ የዜማ ሸክላዎች ብቅ እስካሉ ድረስ፣ የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ሸክላዎች ከ20 አመታት በላይ አቅም ባላቸው ቤተሰቦች ዘንድ በብቸኝነት በግራማፎን ሲደመጡ ቆይተዋል፡፡



## ክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ

ጥላሁን ገሠሠ መስከረም 17 ቀን 1933 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዶ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወሊሶ ከተማ አደገ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር ሙዚቃና ቴአትር ለሕብረተሰቡ ለማሳየት ወሊሶ በተገኘበት ወቅት የጥላሁን ገሠሠ ስሜት ወደ ሙዚቃው ዓለም በመሸፈቱ ትምህርቱን አቋርጦ አያቱ ከወሊሶ ወደ አዲስ አበባ ይዘውት መጡ፡፡ አዲስ አበባም ዶሮ ማነቂያ አካባቢ ከአክስቱ ጋር መኖር ጀመረ፡፡

ጥላሁን ለመጀመሪያ ጊዜ መድረክ ላይ ወጥቶ መዝፈን የጀመረውና ለሕዝብ የታየው በ1946 ዓ.ም ነበር፡፡ ሕይወቱን በሙሉ በሙዚቃ አለም ያሳለፈውና ሰፊ ልምድ ያካበተውም በቀድሞው የክብር ዘበኛ /ማዕከላዊ ዕዝ/ ውስጥ ነበር፡፡ ጥላሁን በተለያዩ መድረኮችና በካሴት ዜማዎቹን በማቅረብ የሕዝቡን የሙዚቃ ጥማት ለማርካት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

ጥላሁን ገሠሠ በእንጉርጉሮው ያልዳሰሰው ጉዳይ የለም ለማለት እንደፍራለን ስለፍቅርና ጥላቻ፣ ማግኘትና ማጣት፣ በሽታና ጤንነት፣ ስለፖለቲካ፣ ስለሀገር፣ ስለውበት፣ ጀግንነት ፣ ስለተፈጥሮ፣ ስለማህበራዊ ችግሮችና አጋጣሚዎች ወዘተ... በአጠቃላይ ሁሉንም የሕይወት ፈርጆች ነክቷል፡፡ ለዚህም ጥረቱ የዘፋኞች ንጉሥ ተብሏል፡፡

ዘመናዊ የሙዚቃ አቀራረብ በሀገራችን በጉልህ መታወቅ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በድምፁ ለዛ በአቀራረቡ በቁመናውና በልዩ የማቀንቀን ስልቱ የብዙዎቹን የሙዚቃ አፍቃሪዎች ስሜት የማረከ በብዙ መቶ ለሚቆጠሩ አዳዲስ ድምፃውያን በር የከፈተና ምሳሌ የሆነ አብዛኛዎች ወይም ሁሉም የሙዚቃ ሙያተኛ የሚያደንቁትና የሚኮሩበት ነው፡፡

ጥላሁን ገሠሠ ከ1946-1948 ዓ.ም. በሀገር ፍቅር ቴአትር፤ ከ1948-1978 ዓ.ም በቀድሞው የክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ፣ ከዚያም ከጥር 1 ቀን 1978 ዓ.ም. እስከ ጥር 30 ቀን 1982ዓ.ም. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር በመስራት ላለፉት በርካታ ዓመታት ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ዜማዎችን የተጫወተ መሪ ድምፃዊ ነው:: ጥላሁን ገሠሠ ዜማና ግጥሞችን ራሱም በመድረስ ተጫውቷል ከእነዚህም መካከል «ምግብማ ሞልቷል»፣ «ሁሉንም ነገር ለይቼ አይቼዋለሁ»፣ «እንጉዳዬ ነሽ»፣ «ሞናሊዛ» እና «ተማሪ ነኝ» የተሰኙትን መጥቀስ ይቻላል::

ለጥላሁን ገሠሠ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ ግጥምና ዜማዎችን በመድረስ ተሰፋዬ ለሜሳ፣ ኮሌኔል ሳህሌ ደጋጎ፣ ሻምበል አፈወርቅ፣ ሻለቃ ግርማይ ህድጎ፣ ገብረአብ ተፈራ ፣ተዘራ ሀ/ሚካኤልና ኑሩ ወንዳፍራሽ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል::



## ግርማ ነጋሽ

ግርማ ነጋሽ የተወለደው በ1936 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ሲሆን ያደገው ደግሞ ከፍልውሃ በላይ ፊት በር ከሚባለው ሠፈር ነው ::

ግርማ ነጋሽ ወደ ሙዚቃው ዓለም ለመግባት ዋናው ምክንያት የሆነው ሙዚቃን መውደድ ብቻ ሣይሆን ከታዋቂው ጥላሁን ገሠሠ ጋር በአደጉበት አካባቢ በሠፈር ልጅነት መገናኘትና የቅርብ ጓደኛ መሆን ነው:: መጀመሪያ በፖሊስ ሠራዊት ከዚያም በብሔራዊ ቲያትር በመቀጠር 8 (ስምንት) ያህል ሙዚቃዎችን ተጫውቷል:: ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረክ ላይ ይዞ የቀረባቸው ዘፈኖች « የኔ ሂሣብ »፣ « ምነው ተለየሽኝ » በመባል የሚታወቁትን ነው:: ዜማዎቹ የሌላ ቢሆኑም ለሰሚ ጆሮ ጥሩ ሆነው እንዲደርሱ በአኩሌታ ጥረት ያደረገባቸው በመሆኑ አብዛኞቹን ይወዳቸዋል:: የቤተሰብ ሙያውን ባለመውደድ እና በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሙዚቃን የወደዳትን ያህል ፈጥኖ ሊታወቅባት ችሏል::



# እሣቱ ተሰማ

*በ1931 ዓ.ም. በሲዳሞ ክ/ሀገር ተወለደ ። በ1934 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ዘመድና ረዳት ስላልነበረው በስድስት ኪሎ አካባቢ ጫማ እየጠረገ እራሱን ማስተዳደር ጀመረ። በልጅነት ጊዜው በበዓላትና በሠርግ ላይ በድምፁ ይጫወት ነበር። በ1946 ዓ.ም. መባቻ ላይ በቀድሞው የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ የመጀመሪያ ድምፃዊ ሆኖ ለመቀጠር የበቃውና ከአገራችን ቀደምት የሙዚቃ ሰዎች መካከል አንዱ ሊሆን ችሏል።*

*በ1948 ዓ.ም. በሀገራችን የሬዲዮ አገልግሎት ሲጀምር « እንኩ እንኩ ፅጌረዳ፣ አጥቻት ሳልጉዳ » በሚለው ዘፈኑ የመጀመሪያው ድምፃዊና የሬዲዮ ጣቢያው መራቂ ለመሆን በቅቷል። አንጋፋው ከያኒና ለሀገር ባህል ዜማ ከፍ ያለ ፍቅር የነበረው እሣቱ ከ200 በላይ ዘኖችን የተጫወተ ሲሆን በራሱ ዜማና ድርሰት ተጫውቷቸው በሕዝብ ዘንደ ከተወደዱለት መካከል « ድማሜ » ፣ « ትዳር ስመኝ »፣ እና « ምነው መንገብገቤ » ድንቅ የሥራ ውጤቶቹ ናቸው።*

*እሣቱ በሙያው ኩሩ የነበረና ነባር ድምፃዊ የነበረ ሲሆን በጤናው መታወክ ምክንያት ከሚወደውና ከሚያፈቅረው አሳድጉም እዚህ ካደረሰው የሙዚቃ ክፍል በ1970 ዓ.ም. በሐኪም ፈቃድ ተሰናበተ።*



# ተዘራ ኃ/ሚካኤል

*ተዘራ ኃ/ሚካኤል በ1930 ዓ.ም. በሸዋ ክፍለ ሀገር በየረርና ከረዮ አውራጃ ደብረዘይት ከተማ ልዩ ስሙ ሆራ በተባለው ሥፍራ ተወለደ። ተዘራ በወላጅ አባቱ የሥራ ፀባይ የተነሳ ባሌንና ወለጋን ገና ሕፃን ሳለ ረግጧቸዋል። በ1938 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በዳግማዊ ሚኒልክ ት/ቤት እስከ 9ኛ ክፍል ድረስ ተማረ።*

ከድምፃዊነቱ ባሻገር በጌታር ጨዋታ የተካነ ነው፡፡ በተጨማሪም የዜማና የግጥም ድርሰት ዕጣ ክፍሉ ናቸው፡፡ ተዘራ በአብዛኛው የሚታወቀው በቁመቱ ነው፡፡ ምነው ቢሉ ከሚጫወትበት የጊታር መሣሪያ ከፍ የሚለው በጥቂቱ ነው ፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም የጊታርን ተንዳኝነት የመረጠው፡፡

ተዘራ በረጅም ዘመን ቆይታው ከተጫወታቸው አያሌ ዘፈኖች ውስጥ « እኔ ነኝ ተዘራ» እና « ማን ይሆን ተርጓሚ» የተሰኙት ዜማዎቹ በሕዝቡ ዘንድ እንዲታወቅ አድርገውታል፡፡



## ባህታ ገ/ሕይወት

ባህታ ገ/ሕይወት ሚያዝያ 27 ቀን 1935 ዓ.ም. በትግራይ ክፍለ ሀገር አዲግራት ከተማ ተወለደ ፡፡ በዚያው ከተማ የቅዳሴ ትምህርቱን አስር ዓመት ሲሞላው አጠናቋል፡፡ አባቱ በቅስናው እንዲገፋበት ቢወተውቱትም የእርሱ ምርጫ ግን እንደ አባቱ ስላልነበረ ዘመናዊው የቀለም ትምህርት እስከ 8ኛ /ስምንተኛ/ ክፍል ድረስ በትግራይ ክ/ሀገር ተማረ፡፡ ከፍተኛ ትምህርቱን በመከታተል ነበር፡፡ ጐንደር ጤና ኮሌጅ ገብቶ ትምህርቱን በመተው ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡

ተፈጥሮ የሰጠውን የሙዚቃ ፍቅር ገና ትንሽ ልጅ እያለ ይሞክር ስለነበር ይህንን የተረዱት አስተማሪዎቹ የ4ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት እስከ 8ኛ /ስምተኛ/ ክፍል ድረስ መዝሙር እንዲያስተምር ያደርጉት ነበር፡፡ ባህታ ለሙዚቃ ያለው ፍላጐቱ እያደገ በመሄዱ ከራስ ባንድ የሙዚቃ ክፍል ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ቀርቦ ለመታወቅ በቃ፡፡

ባህታ ከ60 ያላነሱ ዘፈኖችን የተጫወተ ሲሆን ከነዚህም መካከል በተለይ «ደግሞ እንደምን አለሽ »፣ « ሀሎ ሀሎ » ፣ « ተረሳሁኝ እንዴ » እና « ናይ ፍቅሪ ስቃይ » /ትግሪኛ/ የተባሉ ዘፈኖቹ ባህታን ከሚያስተዋውቁት መካከል ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በወቅቱ የነበረው የሙዚቃ ሥራ ቤተሰብ ለመመስረት የሚያስችል ገቢ የማያስገኝ ስለነበረ ባሕታም የሚወደውን የሙዚቃ ሥራ በመተው የሙዚቃው ስሜት አብሮት እያለ ኑሮውን ለማሻሻል ሲል በአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በመግባት በሂሣብ አያያዝ ተመርቆ በዚሁ ሙያ ተሰማርቶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡




## አያሌው መስፍን

አያሌው መስፍን በ1942 ዓ.ም በወሎ ክፍለ ሀገር በየጁ አወራጃ ተወለደ:: አያሌው ገና በልጅነቱ የሙዚቃ /የዘፋኝነት/ ሙያ ፍቅር ስለነበረበት ወላጆቹ ወደ ት/ቤት ሲልኩት እሱ ግን የሚውለው አዝማሪዎች በማሲንቆ በሚጫወቱበት ሥፍራ ነበር:: ይህንንም በውስጥ የሚነደውን የሙዚቃ ፍቅር ለማርካት ጠፍቶ በ1956 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጣ:: አዲስ አበባ እንደመጣም ብሔራዊ ቲያትር ድምፃውያንን ለመቅጠር ማስታወቂያ አውጥቶ በነበረበት ጊዜ የተሰጠውን የመግቢያ ፈተና መቶ ከሚሆኑ ተወዳዳሪዎች በአንደኛነት ቢያልፍም ወላጆቹ በተለይም አባቱ የአያሌውን ዘፋኝ መሆን በሬዲዮ ከሰማ አዝማሪ ሆነ ብሎ ይጠላኛል በማለት ፈርቶ ሳይቀጠር ቀረ:: ከዚያም አባቱ እንዳይቀየሙት በማለት ሙያውን ትቶ በቀድሞው የክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ በወጣት ሻምበልነት ተቀጥሮ እስከ 1959 ዓ.ም. ድረስ ቆየ:: ሆኖም አያሌው ዓላማና ፍላጐቱ በሙዚቃ ሙያ ውስጥ ገብቶ ስሜቱን ማርካት በመሆኑ ወደ ሙዚቃው ዓለም የሚገባበትን መንገድ ቀይሶ በጊዜው በነበረው አንድ ባንድ ውስጥ ተቀጥሮ በ1959 ዓ.ም. ወደ ጅማ ሄደ::

አያሌው ከጅማ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ፈጣን ኦርኬስትራ በመባል በሚታወቀው በወ/ሮ አሰገደች አላምረው ቤት (ፓትሪስ ሉሙምባ የሚባል የማታ ክበብ ውስጥ) በሳምንት አምስት ብር እየተከፈለው ተቀጥሮ ይሠራ ነበር:: ሆኖም ግን በዚያን ጊዜ ማለት በነሐሴ ወር 1959 ዓ.ም. 16 የሚሆኑ ዘፈኖቹን አዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮ አቀረበ:: ከዚያ በኋላ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ፍቅርና አድናቆትን አትርፎ ክፍያው በቀን ወደ አሥራ አምስት ብር ከፍ አለ::

ከዚያም በ1962 ዓ.ም. አያሌው የፈጣን ኦርኬስትራን ትቶ ብሔራዊ ቲያትር ገባ:: ብሔራዊ ቲያትርም ለ3 ወራት ያህል ብቻ ከሠራ በኋላ ክፍሉን ለቆ በፖሊስ ሠራዊት የሙዚቃ ክፍል ተቀጥሮ እስከ 1966 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓል ድረስ ሲያገለግል ቆይቶ ከ1966 ዓ.ም. በኋላ ጥቁር አንበሳ የተባለ የግሉ የሙዚቃ ጓድ አቋቁሞ በ14ቱም ክፍላተ ሀገራት ተዘዋወሮ የሙያ ግዳጁን ተወጥቷል::

አያሌው ከ300 የሚበልጡ ዘፈኖችን የተጫወተ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ « ቻለው ሆዴ»፣ « ማሩኝ ዘመዶቹ »፣ « ማን ልበል ወዳጄ »፣ « በምላስ በስሎ »፣ « አላጉበድድም »፣ « ቀኔን እገፋለሁ »፣ « ወልደሽ ያሳደግሽኝ እናቴ ናፈቅሽኝ » የተሰኙት በሕዝብ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ናቸው፡፡

## እዮኤል ዮሐንስ

ኢዮኤል ዮሐንስ በ1927 ዓ.ም. ተወለደ፡፡ ኢዮኤል ዮሐንስ በመጀመሪያ ዲያቆን እንደነበርና አቶ መኮንን ሀብተወልድ ሲቀድስ ድምፁን ሰምተው በ1935 ዓ.ም. አስጠርተው በሀገር ፍቅር እንዲቀጠር እንዳደረጉትና በድምፃዊነትም፣ በቲያትር ደራሲነት በተፈጥሮው የታደለ በመሆኑ በቲያትር ቤቱ ትልቅ ዝናን ለማትረፍ በቅቷል፡፡




## ግርማ በየነ

ግርማ በየነ አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ ሲሆን ትምህርት ቤት ሲዘጋ በጊዜያዊነት በቀ.ኃ.ሥ.ቲ በድምፃዊነት በመቀጠር በ1952 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ታየ ከዚያም እንደገና የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን በማቋረጥ እስከ 1953 ዓ.ም. ድረስ በራስ ባንድ በሙዚቃ ክፍል በድምፃዊነት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ የራሱን ባንድ በማቋቋም በራሱ ፍቃድ ሥራውን ለቆ ወጣ፡፡



## መስፍን ኃይሌ

በሐረርጌ ከተማ ተወልዶ ያደገ ሲሆን ከዚያም ወደ ዝቋላ መጥቶ የቄስ ትምህርት ተምሮ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የክብር ዘበኛ ሠራዊት ባልደረባ በመሆን ከ1943-1949 ዓ.ም. ድረስ እያገለገለ በመጠኑ ያንጐራጉር ነበር፡፡ በ1950 ዓ.ም. እንደገና የፖሊስ ባልደረባ በመሆን የቲያትርና የሙዚቃ ክፍል አባል ሆኖ በድምፃዊነቱ በመጫወት ጥሩ ዝናን አትርፏል፡፡



## ካሣ ወልዴ

ካሣ ወልዴ ባደረበት የሙዚቃ ስሜት የተነሣ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በ1944 ዓ.ም በድምፃዊነት በመቀጠር ተወዳጅነትን አትርፎአል፡፡ የካሣ ዜማዎች ለረጅም ግዜ ተወደው የሚቆዩ ናቸው፡፡



## ጌታመሳይ አበበ (የማሲንቆው ሲቅ)

ጌታመሳይ በአሩሲ ክ/ሀገር ልዩ ስሙ አልባሶ በተባለ ቦታ በ1935 ዓ.ም. ተወለደ:: ባለመሰንቆው ጌታ መሳይ በሙያው ተለክፎ እጁን ለሙዚቃ የሰጠው ገና አንድ ፍሬ ልጅ ሳለ በሚኖርበት ሠፈር አካባቢ ሠርግና ክርስትና ሲኖር የሙዚቃ መሳሪያ /ማስንቆ/ ይጫወቱ የነበሩትን በማየት ልቡ እጅግ ከተነካ በኋላ ነው:: ጌታመሳይ በግል ጥረቱ እንጨት እያጎበጠ የፈረስ ጭራ በማሠር መሰንቆ መጫወት በመቻሉ ስሜቱ ወደዚህ ሙያ እንዲያመራ አስገደደው:: ጌታመሳይ በ1953 ዓ.ም. ከሀገር ቤት መጥቶ ብሔራዊ ቲያትር ቤት ልምምድ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በአንዳንድ ተፅዕኖዎች ምክንያት ቲያትር ቤቱን ተሰናበተ :: በ1956 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የባህል ማዕከል የኢትዮጵያ ኦርኬስትራ እንደተቋቋመ ተቀጥሮ በርካታ ዘፈኖችን ተጫውቷል:: በ1960 ዓ.ም. ወደ ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ተዛወረ::

ጌታመሳይ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ከዘፋኝነት በተጨማሪም የቲያትር ሙያን ሊማር በመቻሉ ከአስር በላይ በሚሆኑ ቲያትሮች ከዕውቅ አርቲስቶች ጋር በመሆን ሠርቷል:: ለዚህም ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉት በአቤ ጉበኛ « የደካሞች ወጥመድ »፣ በብርሃኑ ዘሪሁን « የለውጥ አርበኞች » እና በጌታቸው አብዲ « ስንት አየሁ » ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው::

ጌታመሳይ እስካሁን ከሁለት መቶ የማያንሱ ዜማዎችን ተጫውቷል:: ከእነዚህም ውስጥ « ሆብዬ እመጣለሁ »፣ « ሀገር መውደድ ማለት »፣ « ዳይመኔ »፣« የመኖሪያ ቤቴ » እና « የኔ ሀያል » የተባሉት ለዛ ያላቸው ዜማዎቹ በአድማጭ ዘንድ ያላቸው ተወዳጅነት ከፍተኛ ነው ጌታመሳይ ያለው የጠለቀ የመሰንቆ ዕውቀትና ችሎታው « የመሰንቆው ሊቅ » የሚል መጠሪያ አጎናፅፎታል:: ጌታመሳይ አበበ መሰንቆን ከምንም ነገር የበለጠ ይወዳል:: ጌታመሳይ አበበ በሰሜን አሜሪካ በአውሮፓና በአፍሪካ በመዟዟር የሀገራችንን የባሕል ጨዋታ በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ላይ ያንፀባረቀ አንጋፋ የባሕል ተጫዋች ነው::



## መልካሙ ተበጀ

መልካሙ ተበጀ  የተወለደው በ1938 ዓ.ም. በሲዳሞ ክ/ሀገር ክብረ መንግስት በሚባል ቦታ ነው፡፡ መልካሙ የሙዚቃ ፍቅር ከሕፃንነቱ ጀምሮ አብሮት ያደገ ነው፡፡ ቤተሰቦቹ ለስራ ጉዳይ ወደ ሐረር ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሲዛወሩ አብሮ በመምጣት በአምኃ ደስታ ት/ቤት ይገባል፡፡ በት/ቤት በተለያዩ በዓላት በተለይም በወላጆች ቀን በሚያደርገው ተሳትፎ የሙዚቃ ስሜቱ ከእሱ አልፎ በተመልካች ዘንድ እየጎላ በመሄድ ነሐሴ 15 ቀን 1957 ዓ.ም. በብሔራዊ ቲያትር የታዳጊ ኦርኬስትራ /ዳዊት ኦርኬስትራ/ በድምፃዊነት ተቀጠረ፡፡

መልካሙ እስካሁን ድረስ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ ከእነዚህም ዜማዎቹ አንድ መቶ ሃምሳ ያህል የራሱ ድርሰቶች ናቸው፡፡ « የሲዳሞ ቆንጆ » ፣« በይ እንግዲህ ተለያየን »፣ « ቸብ ቸብ » ፣ « ዳህላክ » እና «ሙዚቃ »የተሰኙ ዜማዎቹ እራሱ ደርሶ ከተጫወታቸው ዘፈኖች መካከል በዋቢነት ሊዘከሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ መልካሙ ከግጥምና ዜማ ደራሲነቱ ባሻገር ቲያትርም የመድረስና በተዋናይነት የመሳተፍ ችሎታ ያለው አንጋፋ  ከያኒ ነው፡፡ የድርሰት ችሎታውን ካስመሰከረባቸው ስራዎቹ አንዱ የሆነውና እራሱም በተዋናይነት  የተሳተፈበት
« ቢሮክራሲያዊ የከበርቴ አሻጥር » የተሰኘው ድርሰቱ አንዱ ነው፡፡ መልካሙ በበርካታ የቴሌቪዥን ድራማዎች ከመጫወቱ ሌላ በፀጋዬ ገ/መድህን በተደረሰው « አቡጊዳ ቀይሶ » በአያልነህ ሙላት በተደረሰው « ሻጥር በየፈርጁ » እና በሌሎችም ቲያትሮች ተሳትፎአል፡፡

መልካሙ ተበጀ ስለ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለወጣነት ስለ ተፈጥሮ ስለፍቅር እና ስለ ሌሎችም ብዙ የተጫወተ መልከ መልካም አንጋፋ ከያኒ ነው፡፡



## አበበ ተሰማ

አበበ ተሰማ በ1924 ዓ.ም. በሰላሌ አውራጃ ጎሓጽዮን ከተማ አካባቢ ከሚኖሩ ገበሬ ቤተሰብ ተወለደ፡፡ አበበ በአደገበት አካባቢ በእርሻ እና በምንጠራ ስራ ላይ ሲሰማራ ማንጎራጎር ይወድ ነበር ፡፡ በየምንጠራውም እየሄደ ያንጎራጉር ነበር፡፡ በ1942 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በዕደ ጥበብ ማዕከል ውስጥ በሽመና ስራ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር፡፡

በ1953 ዓ.ም. ወደ ሙዚቃው ዓለም ለመግባት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ድምፃዊ ለመቅጠር ማስታወቂያ አውጥቶ ፈተናውን ካለፈ በኋላ በደመወዝ አለመስማማት ምክንያት ተወው፡፡ ከዚያም በአቶ ኢዩኤል ዮሐንስ አማካኝነት ሀገር ፍቅር ማህበር ተቀጥሮ ለ3 ዓመታት ያህል ካገለገለ በኋላ ሀገር ፍቅርን ትቶ በአቶ አውላቸው ደጀኔ አማካይነት በ1957 ዓ.ም ብሔራዊ ቴአትር ተቀጠረ፡፡

አበበ በራሱ ግጥምና ዜማ ከ180 በላይ የሚሆኑ የባሕል ዘፈኖችን በአማርኛና በኦሮምኛ ተጫውቷል፡፡ « ቢሌ ቦምቢሌ » የተባለው የኦሮምኛ ዘፈን « አባይም ቢሞላ » « ልወዝወዘው በእገሬ » እና « ታጠቁ ማለዳ » የተሰኙት ዘፈኖቹ በይበልጥ አስተዋውቀውታል፡፡ አንጋፋው አበበ ተሰማ ድምፃዊ የኢትዮጵያ የባሕል ጨዋታ አምባሳደር በመሆን ወደ ተለያዩ የውጭ ሀገሮች በመሄድ ተሳትፏል፡፡



## ንዋይ ደበበ

ንዋይ ደበበ በጋሞጎፋ ክ/ሀገር በገለብና ሀመርባኮ አውራጃ በሀመር ወረዳ በ1953 ዓ.ም ተወለደ፡፡ በተወለደበት አካባቢ ትምህርቱን እስከ 4ኛ ክፍል ከተማረ በኋላ በ1963 ዓ.ም ወደ አሰላ በመሄድ እዚያው እየተማረ ሳለ በአስተማሪውና በት/ቤት ጓደኞቹ ዘንድ አድናቆትን እያገኘ መጣ፡፡ በኋላም ላይ ነዋይ ወደ ሲዳሞ በመሄድ በአርባምንጭ በወላይታ ኪነት ውስጥ በድምፃዊነት ሊቀጠር ችሏል፡፡ ከዚያም በ1977 ዓ.ም. የመጀመሪያ ካሴቱን ለማሳተም ችሏል፡፡ ንዋይ ከድምፃዊነቱ በተጨማሪም የዘፈን ግጥሞችን ይደርሳል፡፡
« የጥቅምት አበባ በምትሰኘው ዘፈኑም በይበል ይታወቃል፡፡»



## ፍሬው ሀይሉ

ፍሬው ሀይሉ በ1933 ዓ.ም በትግራይ ክ/ሀገር ተንቤን አውራጃ ተወለደ፡፡ ቀደም ሲል በድቁና ሲያገለግል የነበረው ፍሬው በ1947 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ተቀጠረ፡፡ ፍሬው ሀይሉ በሕይወት ዘመኑ ከአንድ መቶ በላይ ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ ከተጫወታቸው ዜማዎች በተለይ « ዐይን የተፈጠረው »፣ « እሸሩሩ »፣ « ሱቅ በደረቴ »፣ « ኑኑዬ ጨቅላዋ » የተሰኙት ውብ ዜማዎቹ አሁንም ቢሆን ተወዳጅነታቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ ፍሬው በአኮርዲዮን አጨዋወት ቅልጥፍናው የሚደነቅ ከመሆኑም ሌላ የሙዚቃ አቀናባሪ ፣ የተዋጣለት ተዋናይ፣ የግጥምና የዜማ ደራሲ ነበር፡፡ ፍሬው በ1949 ዓ.ም አምስት የሚሆኑ የባህል ዜማዎቹን በሸክላ አስቀርፆ ለሕዝብ አቅርቧል፡፡



## አሰፋ አባተ

« ***የማሲንቆው አባት*** »

አሰፋ አባተ በ1929 ዓ.ም በወሎ ክ/ሀገር የጁ ሳንቃ ቀበሌ ተወለደ፡፡ አሰፋ 9 አመት እንደሞላው በድምፁ ግሩምነት ተደንቆ በደሴ ቤተመንግስት ስራ ጀመረ፡፡ ከዘያም በ1941 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በሀገር ፍቅር ማህበር ተቀጠረ፡፡ አሰፋ አባተ በሙዚቃው ዓለም ለአጭር ጊዜ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ 50 የሚሆኑ ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ በዚህ የአጭር ጊዜ ቆይታውም የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስደሰት ከፍ ያለ ዝናን አትርፏል፡፡

አሰፋ ለዛ ባለው አንደበቱ ሲጫወት ያዳመጠውን ሁሉ ከልብ ያስፈነደቀ፣ በመሰንቆ አገራረፉ ማንንም ያስደነቀ፣ በግጥም አጣጣሉ ሴት ወንዱን ያሳቀ፣ ከባህል መልዕክተኞች ጋር

በወዳጅ ሀገሮች ተዘዋውሮ የተጫወተ፣ ዝናው እስከ መቼም ድረስ የማይረሳለት ዕውነተኛ የተፈጥሮ ድምፃዊ ነበር።

አሰፋ አባተ « ዓሳ አበላሻለሁ ዓባይ ዳር ነው ቤቴ » እና « የማትበላ ወፍ በጭራ ተይዛ » በተባሉት ዜማዎቹ በሚያውቁት ዘንድ እስከመቼውም የማይረሳ ነው።



**መርዓዊ ዮሐንስ**

**« አልማዜ »**

አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገው መርአዊ ለሙዚቃ ሕይወት ራሱን የሰጠው ገና የስምንት ዓመት ልጅ ሳለ ነው።

ወላጆቹ በትምህርቱ እንዲተጋ በማሰብ በቀድሞው አስፋወሰን ት/ቤት አስገብተውት ነበር። ሆኖም መርአዊ በዚያን ዘመን ቀደምት የነበሩትን ድምጻውያን በተለይም የጥላሁን ገሠሠን የምኒልክ ወስናቸውንና የግርማ ንጋሽን ድምጽ በሬድዮ በሚያዳምጥበት ወቅት በስሜት አብሯቸው ይመንን ነበር።

መርአዊ የአሥር ዓመት ልጅ እያለ በት/ቤቱ ውስጥ የወላጆች ቀን በዓል ይከበራል። በዚያን ቀን ወላጆችና በርካታ እንግዶች በተሰበሰቡበት በነበረው ቃጭል ድምጽ ልዩ ጣዕም ያለው ዜማ ያሰማል። የሙዚቃ አፍቃሪ የሆኑ ሁሉ ይህን ድምጻዊ በስሙ ሲጠሩት ተሰምቶ አይታወቅም። ገና ልጅ ሳለ « አልማዜ » የምትባለውን ዘፈኑን ስለተጫወተ አድናቂዎቹ ሁሉ መርአዊን « አልማዜ » እያሉ ይጠሩት ነበር።

መርዓዊ ከተጫወታቸው ዘፈኖች መካከል በተለይ «በይ ደህና ሁኚ »፣ « ሸንኰይ እንኰይ»፣ « ሸንደምን ሸሸሸ እህቴ »፣« ሁሱ ጉድ ሸፈሳ»፣ «ውቤ ከረሜላ »፣ «ተለየሽኝ» ፣« አንችን ያዩ ሁሉ »፣ « አትንከኩብኝ» የተሰኙነት ዜማዎቹ ታዋቂ አድርገውተ ነበር።

## ፅጌ ማርያም ገብሩ ደስታ (እማሆይ)

## ( የኢትዮጵያ ክላሲካል ሙዚቃዎች እናት )

እማሆይ ፅጌ ማርያም ገብሩ ከአባታቸው ከከንቲባ ገብሩ ደስታ በአዲስ አበባ ከተማ በ1916 ዓ.ም. ተወለዱ። እማሆይ ትምህርታቸውንም ስዊዘርላንድ ውስጥ በሚገኘው ቅዱስ ክርስትና የሰብአዊ ትምህርትን አጥንተዋል። እማሆይ ፅጌ ማርያም ቫዮሊን መጫወትን ተምረው በ9 ዓመታቸው ትርኢት ለማሳየት ችለዋል።

ህይወታቸው በውጣ ውረድ፣ በስኬትና ውድቀት የተሞላው እማሆይ ፅጌ ማርያም በኢትዮጵያውን ዘንድ እምብዛም አይታወቁም።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ ከመላ ቤተሰባቸው ጋር በመሰደድ የጥቁር አንበሳ ጦር ተቀላቅለው በሽምቅ ውጊያ ሦስት ወንድሞቻቸው ተገድለዋል። ጦርነቱ ሲፋፋምም ቤተሰባቸው በመሉ ተግዘው ወደ ኔፕልስ ጣሊያን በግዞት ተወሰዱ። በእስር ቆይታቸው አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከካቶሊክ መነኮሳት ጋር በመሆኑ በውስጣቸው መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያቆጠቁጥ ምክንያት ሆነ።

ከጣሊያን ሽንፈት በኋላም በካይሮ (በግብፅ) የሙዚቃ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። በ21 ዓመታቸው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ባንድ ዳይሬክተር ሆነው ሠርተዋል። ይህም የሙዚቃ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉበት አስችሏቸዋል።

*« Homeless Wonder, » « The Son of Seam», « The Mad Man's Daughter,» «Mother's Love»* የሚል አርዕስት ያላቸው ሙዚቃዎች ከበርካታ ስራዎቻቸው ውስጥ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ። እማሆይ ፅጌ ማርያም እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ዕብራይስጥኛ፣ አማርኛና ግዕዝን አቀላጥፈው ይናገራሉ። የተለያዩ የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም በተለያዩ ኮንሰርቶች ላይ በማቅረብ የሚገኘውንም ገንዘብ ለድሆች መርጃ አውለዋል።

እንድ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ፍራንሲሊስ ፋልሴቶ የተባለው ፈረንሳዊ የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ሰብስቦ እንደ አዲስ « ኢትፒክስ » የተባለ ሲዲ ባወጣበት ጊዜ ቁጥር 21 ላይ የእማሆይንም ስራዎች አካቷል። ሲዲው በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው ሰፊ ስርጭት አንፃር ስለ እማሆይ ፅጌ ማርያም ቀሪው ዓለም ብዙ አውቋል። ታዋቂ የሆኑ የዓለም የመገናኛ ብዙሀንም ስለ እማሆይ ፅጌ ማርያም ስራዎች ብዙ

ፅፈዋል፡፡ ስራዎቻቸውንም ከእነ ቤትሆቨን ፣ ሲሹማን ፣ ዲቢስ ፣ ለምንዴ ፣ እና ሩትስ ጋር አመሳስሏቸዋል፡፡

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለመጀመሪያ ጊዜ በጀርመን ሀገር በሸክላ እንዳሰቀረፁ ሁሉ እማሆይ ፅጌ ማርያምም ከዓመታት በኋላ የኢትዮጵያን ክላሲካል ሙዚቃዎች በሲዲ በማስቀረፅ ለዓለም ሕብረተሰብ ያስተዋወቁ የመጀመሪያዋ እንስት ሆነዋል፡፡



## ሀይሉ ዲሣሣ

ሀይሉ ዲሣሣ በ1947 ዓ.ም. በወለጋ ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ዳሌ ዳርቦ ጃሮ ቱሉ ሰዓ በሚባለው በቂለም አውራጃ በደምቢ ዶሎ ከተማ ተወለደ፡፡

ተወዳጁ የኦሮምኛ ተጫዋች ሀይሉ ዲሣሣ በ1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሀገር ፍቅር ቲያትር በመቀጠር የኦሮምኛ ግጥምና ዜማን በመድረስ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ድራማዎች ላይ በተዋናይነት ተሳትፏል፡፡ ሀይሉ ተፈጥሮ በለገሰችው ድምጹ እና የአቅም ጥረት ታክሎበት አፍቃሪዎችን እያዝናና ይገኛል፡፡ እስከ አሁንም ሰባት የተለያዩ የኦሮምኛ ካሴቶችን አሣትሟል፡፡ በተቀጠረበት በኢትዮጵያ ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤትም በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡



# በሻህ ተክለማሪያም

አቶ በሻህ ተክለማሪያም ከአባታቸው ከግራዝማች ተክለማርያም አጥናፌ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ የሺወርቅ ወልደ ጻዲቅ መጋቢት 1912 ዓ.ም. በባሌ ክፍለ ሀገር በጎባ ከተማ ተወለዱ፡፡ በ4 ዓመት ዕድሜያቸው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የቤተ ክህነት ትምህርታቸውን ጀምረው ሣይጨርሱ በ8 ዓመት ዕድሜያቸው በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በመግባት ዘመናዊውን ትምህርት ገብይተዋል፡፡ በድምጻ ሽጋነታቸው የሚታወቁት በሻህ ተክለማርያም በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ዘመናዊ የሙዚቃ ትምህርት ሲጀመር ትምህርታቸውን በመከታተል ቫዮሊንና ፒያኖን መጫወት ቻሉ፡፡ ጠላት አገራችንን ሲወር በሻህ ተክለማርያም ከፍተኛ እሥርና እንግልት ደርሶባቸው ነበር፡፡ ከጠላት ወረራ በኃላም አቶ በሻህ አርቲስቶችን በመመልመል የተለያዩ የኪነ ጥበብ ትርኢቶችን ከማዘጋጀታቸውም ባሻገር ለአገራችን ኪነ ጥበብ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ድምጽ መቅረጫ /ቴፐሪኮርደር/ ባልነበረው ጊዜ የዜማና የውዝዋዜ መሪ በመሆናቸው ተጫዋቾችን እስቱዲዮ ድረስ በመውሰድ በቀጥታ ዘፈኑን ለሕዝብ እንዲተላለፍ ያደረጉ ሲሆን በኋላም ማስታወቂያ ሚኒስቴር ቴኘ ሪኮርደር ሲያመጣ ዘፈኖችን በማሰባሰብ ቀርጸው ለትወልድ እንዲቆዩ ታሪካዊ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በሻህ ተክለማሪያም የሙዚቃ ዜማ ደራሲ እና አቀናባሪ እንዲሁም የባህልና የዘመናዊ ሙዚቃን ያደራጁ ቀዳሚ ሰው ነበሩ፡፡ በሀገራችን ለሚገኙ ቴያትር ቤቶችና የኪነ ጥበብ ተቋማት የተቀናበረ የሃገረሰብ ሙዚቃ የመጀመሪያው ዘር የዘሩ ነበሩ፡፡




## ፀሐዬ ዮሐንስ

በ1954 ዓ.ም. በኤርትራ /አሥመራ/ ተወለደ:: ፀሐዬ ከወላጅ አባቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ትምህርቱን በሚከታተልበት ወቅት የሙዚቃ ችሎታውን ለማዳበር ቻለ:: የ5ኛ ክፍል ተማሪ አያለ በአብዮቱ ወቅት 60 ሺህ ተማሪዎች ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለዕድገት በሕብረት ዘምተው ሳለ «በርታ ዘመዴ ዘማቹ ጓዴ» የተሰኘው የመጀመሪያውን ሙዚቃ ለሕዝብ በማቅረብ በወቅቱ ከፍተኛ አድናቆት ተችሮታል::

ፀሐዬ በዚህ ብቻ አላበቃም:: መሀይምነትን ለማጥፋት የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በታወጀበት ጊዜ « ማንበብና መፃፍ » የተሰኘው ዘፈኑ በጣም ቀስቃሽና አስተማሪ ስለነበር ፀሐዬን ይበልጥ እንዲታወቅ አድርጎታል::

ከእነዚህም ማህበራዊ ሕይወትን ከሚገልፁት በተጨማሪ በ1975 ዓ.ም. ካሰማቸው ዘፈኖቹ ውስጥ « ፍንጭቷ» ፣ « ያዝ ያዝ » እና « ጡር ነው » የተሰኙት በሕዝቡ ዘንድ ውዴታን ያገኙ ነበሩ:: ፀሐዬ አሁንም ቢሆን የተለያዩ ዜማዎችን በመዝፈን በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት ያለው አርቲስት ነው ::




## ታምራት ሞላ

ታምራት ሞላ በ1939 ዓ.ም. በጎንደር ክ/ሀገር ተወለደ:: ታምራት የ1ኛ ደረጃ ትምህርቱን እዚያው ጎንደር ከጨረሰ በኃላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አድቬንቲስት ሚስዮን ት/ቤት በመግባት ትምህርቱን ተከታተለ:: በ1951 ዓ.ም. በቀድሞ ክብር ዘበኛ በወታደርነት በመቀጠር እስከ 1954 ዓ.ም. ጃዝ፣ ሳክስፎንና ሌሎችንም የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት ጀመረ:: በድምፁም ጭምር ስሜቱን ለማርካት በ1955 ዓ.ም. በምድር ጦር ኦርኬስትራ ተቀጠረ:: ታምራት ለመጀመሪያ ጊዜ ካዜማቸው ዘፈኖቹ « ታምሜ ተኝቼ »፣ « ዘወትር ብርቅነሽ » የተሰኙትን ዘፈኖቹን ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረክ ላይ ሲያሰማ በተመልካቾች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን አትርፈውለት ነበር::

ታምራት እስካሁን ድረስ የዘፈናቸው ዘፈኖች በርካታ ቢሆኑም « አስታውሺኝ »፣ « መሞት አለ ለካ »፣ « የለችም » እና « ጊዜው ለጨነቀው » የተሰኙት ዜማዎቹ የተዋጣላቸው ከመሆናቸው ባሻገር በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ናቸው፡፡



## መሐሙድ አህመድ

መሐሙድ አህመድ አዲስ አበባ አሜሪካን ግቢ አካባቢ ( መርካቶ ) በ1933 ዓ.ም. ተወለደ፡፡ በየዓመቱ በሚመጣው የቡሄ ጨዋታ ላይ የድምፁን ምንነት ያሳወቀው መሐሙድ በወቅቱ እነ ጥላሁን ገሠሠ የሚያሰሙትን ዘፈን በሚማርበት የአርበኞች ት/ቤት ውስጥ ሲዘፍን የሰሙት አስተማሪው ድምፁን ስለወደዱለትና በየዓመቱ በሚከበረው የወላጆች ቀንም ይዘፍን ስለነበር ወደ ሙዚቃው ዓለም በዚሁ የተነሳ ለመግባት ችሏል፡፡

እነ ጥላሁን ገሠሠ ፣ ታምራት ሞላ፣ ተዘራ ኃ/ሚካኤል እና ሌሎችም በሚጫወቱበት አሪዞና በሚባል የምሽት ክበብ ውስጥ በሌላ ስራ ተቀጥሮ ይሠራ ስለነበር የእነዚህን አንጋፋ ዘፋኞች ሙዚቃ በማጥናትና በመዝፈን ይጫወት ስለነበር የዘፈን ችሎታውን ያዩት የምሽት ክበቡ ባለቤት ( ግብፃዊ ) አበረታትተውት እነ ጥላሁንን በማጀብ እንዲሠራ ፈቀዱለት፡፡ ሻለቃ ግርማ ሀድጉ ግጥምና ዜማ ፈልገው አውጥተውለት የመጀመሪያውን « ጭቅጭቁ ቀርቶ » የሚለውን ዘፈን ዘፈነ፡፡

ከዚያም ኦሪዞና የሚባለው የምሽት ክበብ ሲዘጋ « ሾፌሮች » ቡና ቤት ወደ ሚባለው የምሽት ክበብ በመሄድ የነ ገላን ተሰማና፣ የታምራት ሞላን ዘፈኖች ሲጫወት ለመቀጠር እንዲችል በአዳራሹ ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ ለፍርድ ይቀርባል፡፡ በዚህን ጊዜ « ተስፋ አትቁረጪ » እና « የቡጊ ጨዋታ » የተባሉትን ዘፈኖች ደጋግሞ ተጫውቶ ለመቀጠር ቻለ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ጃንሜዳ በሚገኘው የክብር ዘበኛ የሠራዊቱ ሆስፒታል ውስጥ ለሠራዊቱና ለቤተሰቦቻቸው በየ15 ቀናት የሙዚቃ ትርኢት ስለሚቀርብ ከዚያም ለድጋሚ ፈተና ቀርቦ በ1955 ዓ.ም. በሲቪልነት ተቀጠረ፡፡ መሐሙድ ካለፈባቸው የችግር ሕይወት በተጨማሪ የክቡር ዘበኛ ኦርኬስትራ ትልቁ ት/ቤቱ እንደነበረም ይናገራል፡፡

የመሐሙድ የመጀመሪያ ዘፈኑም « አላወቅሽልኝም » የተባለው የጉሮሮው መክፈቻ ሲሆን « ጠይቀሽ ተረጂ » « የፍቅር አዳራሽ » የተባሉት ዘፈኖቹም ለመድረክ ከመቅረባቸው በፊት ለግሩንዲንግ ተሸጠው በቴኘ የተቀረፁ ስራዎቹ ነበሩ::
መሐሙድ በድምፁ ታላቅነት በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በአውሮፓ ትልቅ ክብርና ዝና ያለው አርቲስት ነው::

# ገላን ተሰማ

ገላን ተሰማ ተወልዶ ያደገው በወለጋ ኖኖ ሲሆን፣ ወደ አ.አ የመጣው በአስር ዓመቱ ነው:: በ1947 ዓ.ም. በክብር ዘበኛ ጋራዥ ክፍል ተቀጥሮ ሲሰራ ቆይቶ ከሶስት ዓመታት በኋላ ወደ ቲያትር ክፍሉ ተዛውሮ በመሰልጠን ዳንኪረኛ ለመሆን ችሏል::

ገላን እስከ ዛሬ ድረስ የተለያዩ ዜማዎች ተጫውቷል ከእነርሱም መካከል « እንደ ተመኘኋት » የተባለችውን ዜማ በይበልጥ ይወዳታል፤ ገላን በወቅቱ የክብር ዘበኛ አርቲስቶች የዳንኪራ መምህር ነበር:: ገላን በዳንኪርተኛነቱ እጅግ የተደነቀና የተፈጥሮ ስጦታ ያለው ነው::




# ተፈራ አቡነ ወልድ

ተፈራ አቡነ ወልድ በ1928 ዓ.ም. በደብርብርሃን በተጉለት አውራጃ ተወለደ::

በማዘጋጃ ቤት ተፈራ በትምህርት ላይ ሳለ የሙዚቃ ስሜት ስላደረበት በ1930 ዓ.ም በ17 ዓመቱ በማ/ቤት ተቀጥሮ በዚሁ ሙያ ላይ ዘለል ያለ ችሎታ ለመጨበጥ ችሏል::

በፒያኒስትነቱ የተደነቀ፤ ሲጫወት በሙዚቃ አጨዋወቱ ባቀማመጡና ባቀራረቡ የታወቀው ዕውነተኛ የሙዚቃ ተሰጥዖ ያለው ባንድ ጊዜ ሁለት መሣሪያ እያፈራረቀ መጫወት የሚችል ነው:: ተፈራ ፒያኒስት ከመሆኑም በፊት (ፍሉት) ዋሽንት፣

ክላርኔት፣ ሳክስና አልቶን በማፈራረቅ ተጫውቷል። በዚህም ችሎታው ተመርጦ ፒያኒስት እንዲሆን ተደረገ ።

ተፈራ በሙዚቃ ማዋሃድና በዜማ መድረስም ሰጦታ ያለው ፤ ዜማን ከሸክላ በቀጥታ መገልበጥ የሚችል ባለሙያ ነው ፤ ከደረሳቸውም ዜማዎች « የአባይ ውሃ »፣ « የዓይን ተስፋ » እና « እምነሸነሻለሁ » የተባሉት ይገኙበታል።

ተፈራ የሙዚቃ የባሕል መልክተኖቻችን በሄዱበት አገር ሁሉ ተዘዋውሮ በመጫወት የተደነቀ ቁንጮ ከምንላቸው ሙዚቀኞቻችን አንዱ የሆነ ፒያኒስት ነው።

## ታጠቅ ገ/ወልድ

## 1928- 2001

ታጠቅ ገ/ወልድ በ1928 ዓ.ም በሸዋ ሰላሌ ጅሩ ተወለደ። ታጠቅ ባደረበት የሙዚቃ ዝንባሌ የሀገር ባህል ሙዚቃ ክፍል በተለይም ማሲንቆን በመጫወት የሚታወቅ ሲሆን ዜማዎችንና ግጥሞችንም በመድረስ የሚታወቅ አንጋፋና ታዋቂ አርቲስት ነበር።




# ተፈራ ካሣ

ተፈራ ካሣ የዘፈን ስሜት ያደረበት ገና በልጅነቱ በበረሃ እረኛ ሆኖ ከብቶች በሚጠብቅበት ወቅት ነበር። በጓደኞቹ ዘንድ በድምፁ እየተመረጠ ለሆያሆዬ፣ ለጥምቀት፣ ለዘመን መለወጫና ለመሳሰሉት በዓላቶች አውራጅ ነበር።

በ1945 ዓ.ም. ወደ አ/አ መጥቶ በክብር ዘበኛ ወታደርነት ተቀጠረ፡፤ ከዚያም ወደ ቴያትር ክፍሉ ተዛውሮ ድምጻዊ ለመሆን በቃ።

በልጅነቱ ሲዘፍን ወላጆቹ አሰደብከን፣ ዘራችንን አበላሸኸው እያሉ ይቆጡት ነበር፣ ነገር ግን በሙያው እያደገ ሲመጣና ሙያው በሌሎች አገር እጅግ የሚደነቅ መሆኑንና

በእኛም አገር እየታወቀ መሄዱን ደጋግሞ ስለነገራቸው ባሁኑ ጊዜ ስለሙያው ያላቸው ግምት መለወጡን ገልፇል፡፡

ተፈራ ካሣ ወደ 60 የሚጠጉ ዜማዎችን እራሱ ደርሶ በዛ ያሉ ደግሞ ከሰው የተደረሱለትን ዜማዎችንም ተጫውቷል፡፡ እራሱ በመጣጣር የአኮርዲዮን መሣሪያ በጥሩ ችሎታ መጫወት ችሏል፤

ተፈራ ረቂቅ የተፈጥሮ ድምፅ ያለው፣ ረጋ ብሎ የሚያዜም፣ በብዙዎቹ ዘንድ የመወደድን ፍቅር ያተረፈ፣ አንገቱን ደፋ አድርጎ የሚታይ፣ ዝምታ ተፈጥሮው የሆነ ግሩም ድምጻዊ ነው፤ በዚህም ችሎታውና ተግባሩ የተነሳ ስሙ በመላው ኢትዮጵያ የታወቀ ሊሆን ችሏል፡፡



# መርዓዊ ስጦት

መርዓዊ ስጦት ልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይጫወታል፣ ዜማ ይደርሳል፣ ከሙዚቃም ያዋህዳል፡፡ በሙዚቃና በቴያትር ጥበብ ሕይወት ላይ የምንገኝ ሁሉ የረጅም ዘመን ድካም አድርገናል ወደዚህ ሕይወት የተመራነው ለስሜትና ለጥቅም ብቻ ሳይሆን ጥበቡም በሀገራችን እንዲስፋፋና እንዲታወቅም ለማድረግ ጭምር ነበር፡፡ ሙዚቃ ሲሰሙት የሚያስደስተውን ያህል ሲሠሩትም ከፍተኛ ድካም ይሰጣል፤ ሆኖም ይህን የሚረዱት የሙዚቃ ትምህርት ምን ያህል ከባድ መሆኑን በቅርብ በሚያውቁና አስተዋይነት ያልጐደላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡



ጌታቸው መኩሪያ

# ጌታቸው መኩሪያ

ጌታቸው መኩሪያ ለሙዚቀኛነት የተቀጠረው በ1942 ዓ.ም. ነው፡፡ የቴኖርን ሙዚቃ ድምፅ የሚወደው ጌታቸው መኩሪያ የሙዚቃ መሳሪያውን ይዞ እየተቁነጠነጠ «አልማዝ ምን እዳ ነው»፣ « ሽለላ » ና የመሳሰሉትን በሚጫወትበት ወቅት ከማስደሰቱ የተነሳ ከሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ የመወደድን ዕድል ለማግኘት ችሏል፡፡ በችሎታው ብዙ አገሮችንም ጐብኝቷል፣ በጉብኝቱም ወቅት ባጨዋወቱ ተደንቋል፡፡



ሙሉቀን መለሰ ሙዚቃ እንደጀመረ

# ሙሉቀን መለሰ

ሙሉቀን መለሰ በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ገና ፲፫ ዓመት ልጅ ሳለ ድምጻዊነት ሙያውን በፈጣን ኦርኬስትራ በመጀመር በ፲፱፻፷ ዓ.ም. አሁን ወደሚገኝበት ወደ ፖሊስ ኦርኬስትራ ክፍል ገብቶ ዝነኛነቱን አሳውቋል ፡፡ ሙሉ ቀን በሙዚቃ ዓለም በነበረበት ጊዜ በርካታ ዜማዎች የተጫወተ ሲሆን ዜማዎቹም በሸክላ ተቀርጸው ወጥተዋል፡፡

« እናቴ ስትወልደኝ መች አማከረችኝ፤ የፊት ጉዴን ትታ እደግ ማሞ አለችኝ » የተባለችው ዜማ የመወደድዋን ያህል ድምጻዊው ሙሉቀን መለሰም ተደናቂ ሁኗል፡፡ ሙሉ ቀን መለስ እንደዚሁም፡- « ወንበር ተደግፎ ክብ ጠረጴዛ የሰነፎች በትር ትችት

በጣም በዛ » እያለ የሚጫወታት ዘፈንም ሙሉቀንን ታዋቂና ዘፈኖቹንም ተወዳጅ አድርጎታል፡፡



# በኃይሉ እሸቴ

በ1957 ዓ.ም. በፖሊስ ሠራዊት ሙዚቃ ክፍል አገልግሎቱን የጀመረው የጠይም ሸንቅጥ በኃይሉ እሸቴ ከድምጻዊነት ችሎታው በላይ ጠቃሚ መልእክት ያዘሉ ግጥሞች ከነዜማቸው በመድረስ ተደናቂ ነው፡፡

በኃይሉ እስካሁን ካቀረባቸው ዜማዎች « ኮሳሳ ጎጆዬ » ና « የጥቁር ድምፅ » የተባሉት ዘፈኖች በሕዝብ ዘንድ የተወደዱ ናቸው፡፡ « የኪዎስኳ እመቤት » የተባለችው የራሱ ድርሰት የበለጠ ዝና አስገኝታለች፡፡



# ለማ ገ/ሕይወት

የቡልጋው ተወላጅ ለማ ገ/ሕይወት በሀገር ባሕል ዜማ የታወቀና በተለይም ኃይለኛ የሆነ ድምፅ ያለው ድምጻዊ ነው፡፡

ለማ በ1942 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተቀጥሮ በሙያው ተደንቆና ብዙ የወዳጅ አገሮችንም ጉብኝቶ በሕዝብ ዘንድም በመታወቁ ተደስቶ የኖረ ሰው ነበር፡፡ ለማ ብዙ ዜማዎች ደርሷል፣ ከእነርሱም መካከል « ያዘው ጉበዝ » የተባለው እና የሠርግ ዘፈኖቹም በሕዝብ ዘንድ በጣም ይወደዳሉ፡፡ የለማ ልዩ ስጦታው በሽለላ ላይ ያዘነበለ ነው፤ ድምፁ ያለ ድምፅ ማጉያ የጐላ ነው፡፡

ለማ ከ፲፯ ዓመት ዕድሜው እስከ ፵፪ ዓ.ም. ድረስ በጦር ሠራዊትና በክብር ዘበኛ ወታደርነት ተቀጥሮ አገልግሏል፤ « የዜማ ፍቅር የያዘኝ በሕፃንነቴ ወራት በደን ከብቶችን በምጠብቅበት ወቅት እንደ ቀረርቶ የመሳሰሉትን ሳንጐራጉር ነበር » ሲል እራሱን

አስተዋውቋል፤ ለማ ከድምጻዊነቱም በላይ « አይረሳም» በሚል አርእስት ስለኢትዮጵያ አርበኞች ታሪክ በግጥም የሚታወስ መጽሐፍ ደርስዋል፡፡



# አሉላ ዩሐንስ ( ስንታየሁ )

ድሬዳዋ ተወልዶ ያደገው አሉላ ዩሐንስ ዕድገቱ በአዳሪ ት/ቤት ውስጥ ነበር፡፡ በዚህ አዳሪ ት/ቤት ውስጥ እያለ የሙዚቃ ስሜት አድሮበት መጫወት ጀመረ፡፡

ከሙዚቃ መሳሪያዎች ጊታር በደንብ መጫወት የጀመረው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ትንሽ እንደቆየ ነበር፡፡ በ1950 ዓ.ም. መጨረሻዎች ለትምህርት ወደ ጀርመን ሀገር ሄደ፡፡ ከዚያም ለሦስት ዓመት ተኩል የሕክምና ትምህርቱን ከተማረ በኃላ በማቋረጥ ወደ ኮንሰርቫቶሪ የሙዚቃ ት/ቤት ገባ እዚህ የሙዚቃ ት/ቤት እያለም '' Mr president '' የተባለውን የመጀመሪያውን ሸክላ አሳተመ፡፡

አሉላ ወደ አሜሪካ በመሄድ ከሁለት አልበሞች በተጨማሪ አራት ሸክላዎች አሳትሟል፡፡ አሉላ በአሥራ አንድ ቋንቋዎች ይጫወታል፡፡ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ እንግሊዝኛ ፣ ስፖንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛና ኢብራይስጥኛ ወዘተ... አቀላጥፎ ይናገራል፡፡ ድሬዳዋ እያለ ስንታየሁ ይባል ነበር ፡፡ « *ስንታየሁ* » የምትባለውም ሙዚቃ ከሕዝብ ጋር አስተዋወቀችው፡፡ አሉላ ከ30 ዓመታት በላይ ረጅም የሙዚቃ ሕይወት ያለው አርቲስት ነው፡፡

አሉላ ቮካሊስት ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ጊታር፣ ኪቦርድ፣ አርሞኒካ፣ ድራምንና ፒያኖን በደንብ የሚጫወት ሁለገብና ዘመናዊ አርቲስት ነው፡፡



## ኪሮስ ዓለማየሁ

ኪሮስ ዓለማየሁ በ1948 ዓ.ም. በትግራይ ተወለደ፡፡ ኪሮስ የመጀመሪያና 2ኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በአፄ ዮሐንስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ለ3 ዓመታት በመምህርነት አገልግሏል፡፡ ከዚያም ለሙዚቃ ባለው ዝንባሌ በራሱ ዜማና ግጥም ደራሲነት የትግሪኛ ጨዋታዎችን ለሰፊው ሕዝብ በማቅረብ እና በክራር ተጫዋችነቱ ከፍተኛ ተወዳጅነትን አግኝቷል፡፡

ኪሮስ በ1975 ዓ.ም. በራስ ቲያትር ቤት ተቀጥሮ ከመስራቱ በፊት የትግራይ ክ/ሀገር የኪነት ቡድን ረዳት አሰልጣኝ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ኪሮስ በሀገር ውስጥ ከሚጫወታቸው አዝናኝ የትግርኛ ዘፈኖች በተጨማሪ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን በውጭ ሀገር ማለትም በሊቢያና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራችንን በመወከል ተዘዋውሮ ሠርቷል፡፡




## ዓለማየሁ እሸቴ

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ዘፈን ድምፃውያን ታሪክ ዝናና አድናቆት ያተረፈው ቁመተ ደልዳላው አለማየሁ እሸቴ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአርበኞች ት/ቤት ተከታትሎ ባደረበት ጥልቅ የሙዚቃ ስሜትና ባለው ግሩም ተሰጥኦ ተገፋፍቶ ድምጻዊነቱን በፖሊስ ሠራዊት ሙዚቃ ክፍል ጀመረ፡፡

ቀደም ሲል « እዩዬ »፣ « ማሪኝ ብዬሻለሁ » በተሰኙ ዜማዎቹና « ስቀሽ አታስቂኝ »፣ «ማን ይሆን ትልቅ ሰው »፣ « እንደ አሞራ ክንፍ አውጥቼ ልብረራ» በሚላቸው ዘፈኖቹ በብዙዎቹ ዘንድ የታወቀ አርቲስት ነው፡፡ ለሚስቱና ለልጆቹ

ማቆላመጫ « ውዷ ባለቤቴ! » የምትል ዜማ ተጫውቷል፡፡ **ዓለማየሁ እስካሁን ከ62 በላይ** ዜማዎቹ በሸክላ ተቀርጸው ፲፭ ሺህ ያህሉ ተሸጠውለታል፡፡

ብዙዎቹ የዓለማየሁ ዘፈኖች ከስሜት በሚያፈልቃቸው ዜማዎች ዘመናዊነት የሚታይባቸውና ከውጭ ሀገር ዘፈኖች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

## አባይ በለጠ

ለስላሳ ወይም የትካዜ ዜማዎች በመጫወት የታወቀው አባይ በለጠ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. አሪዞና በሚባለው የማታ ክበብ በድምፃዊነት ተቀጥሮ ድምፁን ከሙዚቃ ጋር ሲያርቅ ከቆየ በኋላ በዚያው ዓመት በጦር ሠራዊት ሙዚቃ ክፍል በድምጻዊነት ተቀጥሮ ለ፲፱፻፶፭ ዓ.ም. መግቢያ እንቁጣጣሽ በዓል በመድረክ ላይ ወጥቶ በሕዝብ ፊት መጫወት ጀመረ፡፡

እስከ ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ድረስ ፲፫ ያህል ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ ከእነርሱም መካከል « የአዲስ አበባ ውበት »፣ « ምነው ብታስቢ » እና « ሳገኝ ከተፍ ያለች » የሚባሉት ይገኙበታል፡፡ ሙዚቃን እንዲወድ በይበልጥ ስሜት ያደረበት እራሱ መጫወት ከጀመረ በኋላ እንደሆን ይናገራል፡፤ አባይ በለጠ ድምፁ ለሰለስ ብሎ ከጆሮ የሚጠልቅ ግሩም ድምጻዊ ነው፡፡



# ምኒልክ ወስናቸው

## *(ጋሽ ጆምበሬ)*

በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዶ ሐረርጌ ያደገው ምኒልክ ወስናቸው የ፪ኛ ደረጃ ትምህርቱን አጋምሶ ለ፭ ዓመታት ያህል በፈረንሣይ ትምህርት ቤት ካጠና በኋላ በ18 ዓመት ዕድሜው በቀ.ኃ.ሥላሴ ቲያትር ቤት በድምፃዊነት ተቀጠረ፡፡

ምኒልክ የመድረክ ላይ ጧፉን « አልማዝ እያሰብኩሽ » በሚል ምርጥ ዜማ ከአበራ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈጣን የሆነ የኪነ ጥበብ ሰውነቱን በማስመስከር አንቱ ከሚያሰኝ ደረጃ ደርሶ ነበር።

የኢትዮጵያን ባህልና ሙዚቃ ስልት በሱዳን፣ በኡጋንዳ፣ በታንዛኒያ፣ በኬኒያ፣ በሶቭየት ሕብረትና በአሜሪካ በመሳሰሉት አገሮች በመዘዋወር ያስተዋወቀ የባህል አምባሳደር ነበር።

ምኒልክ የሚደነቀው ቀደም ሲል ባቀረባቸው የአማርኛ ሙዚቃዎቹ ብቻ ሳይሆን የተዋጣለት አለም አቀፍ ወይም በሙዚቃ ባለሙያዎች አጠራር የኦፔራ ዜማዎችን የሚጫወት ልዩ ተሰጥዖ የነበረው የኪነጥበብ ፈርጥ ሲሆን ቀደም ሲል በሸክላ በካሴትና በሲዲ ያስቀረባቸው ሙዚቃዎች ለትውልድ የሚተላለፉ ቅርሶች ሆነው ሲዘከሩ ይኖራሉ።

ምኒልክ የብሔራዊ ቲያትር ቤት የድምፃውያን ቁንጮ የነበረ ሲሆን ቆየት ሲል ካቀረባቸው ዜማዎች « አፈር አትንፈጊኝ » የተሰኘው እና ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ከዘፈናቸው ውስጥ « እትት በረደኝ ፣ ፍቅር ይበርዳል እንዴ » እና « ጋሽ ጀምበሬ » የተሰኙ ከፍተኛ ተደማጭነትን አግኝተዋል።



ሙላቱ አስታጥቄ
*« የኢትዮ ጃዝ አባት »*

አንጋፋው አርቲስት ሙላቱ አስታጥቄ ***ኢትዮ ጃዝ*** የተባለውን የሙዚቃ ስልት በመፍጠር የሀገራችንን የጃዝ ሙዚቃ ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሰ ታላቅ ሰው ነው። ሙላቱ በዚህ ሥራው ከመወደዱና ከመደነቁም ሌላ በዓለም ላይ ብዙ የኢትዮ ጃዝ አፍቃሪዎችን አፍርቷል። በሥራውም የአብራውዝ ግራንት አሸናፊ ሆኖል።

ኢትዮ ጃዝ ሃርቫርድ የደረሰና አሉ የተባሉ ታላላቅ መድረኮች ላይ መሥራት የተቻለ የሙዚቃ ስልት ነው ። ሙላቱ በበርክሌይ ኮሌጅ የአፍሪካን እስኩልስ አማካሪነትን / የኢትዮ ጃዝን በማክበር/ ሹመት ያገኘ ሰው ነው። ሙላቱ አስታጥቄ *«ብሮክን ፍላወር »* የተባለው ፊልም ላይ ሙዚቃ በመሥራት ትልቅ አድናቆትን አግኝቷል። ይህም ለኢትዮ ጃዝ ሙዚቃ ዕድገትና በዓለም ላይም ትልቅ ደረጃ እንደያገኝ ረድቶቷል።

በ«ቢ.ቢ.ሲ.ና በአፍሪካ ሰማይ ስር» በተሰኙት ኘሮዳክሽኖች አማካይነት በጃዝ ሙዚቃ የተሠሩት በጣም ከባድ የሆኑት መዲናና ዘለሰኛ ስልቶችን በመስራት አስደናቂ ከመሆኑም ሌላ ሙላቱን ምን ያህል የፈጠራ ሰው እንደሆነ ያመላክታል።

## የኢትዮጵያን የባህል ሙዚቃ መሣሪያዎች እናስተዋውቃችሁ

### *የጅማት ሙዚቃ መሣሪያዎች*

እነዚህ መሳሪያዎች ድምጽ የሚሰጡት በንዝረት ነው።

1. በገና፡ መንፈሳዊ ዜማዎችን ለማዜም በሀገራችን ስንጠቀምበት የቆየ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።
2. ክራር፡ ይህ የጅማት የሙዚቃ መሣሪያ ለአያሌ ዓመታት በሀገራችን ለደስታ፣ ለትካዜ፣ ለፍቅርና ለቀረርቶ ሰንጠቀምበት የቆየ መሣሪያ ነው።
3. መሰንቆ፡ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኝ ጥንታዊ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።
4. ዲታ፡ በሲዳሞ የሚገኝ የጅማት መሣሪያ ነው።
5. ዱል፡ በጋምቤላ የሚገኝ የጅማት መሣሪያ ነው።

### *የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎች*

እነዚህ መሣሪያዎች ድምጽ የሚሰጡት በትንፋሽ ኃይለ ነው።

6. ዋሽንት፡ አብዛኛውን ጊዜ እረኞች በሀገር ቤት ይገለገለበታል። በተጨማሪም በመድረክ ላይ ለክራርና ለመሰንቆ ቅኝት በመስጠትና ዜማን በማጀብ ያገለግላል።
7. አምቢልታ፡ ሶስት ዓይነት አመቢልታዎች አሉ ሰማቸውም ኡፍን ፣ አውራ፣ የማ በመባለ ይታወቃሉ። በሀገራችን ለክብረ በዓልና ወደ ጦር ሜዳ ለሚሄድ ሰልፈኛ የሚነፋ አድማቂ መሣሪያ ሆኖ ቆይቷል።
8. መለከት፡ ቀደም ባለው ጊዜ ሰዎች ተሰብስበው የመንግሥት አዋጅ እንዲሰሙ ትዕዛዝን መስጫ መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ነው።

9. ድንኬ፡ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በወላይታ አካባቢ ለአስከሬን ማጀቢያነት የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡
10. ፖረሬሳ፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ለዘፈን ማጀቢያ የሚያገለግል መሣማሪያ ነው፡፡
11. ሁራ፡ በከፋ ክፍለ ሀገር ያሉ ጐሳዎች የሚጠቀመበት የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡
12. ሁልዱዱዋ፡ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የቀብር ሥነ ሥርዓት ለመግለጽ የሚነፋ መሣሪያ ነው፡፡
13. ጨቻ ዝዬ፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ውዝዋዜ ለማድመቅ የሚጠቀመበት የሙዚቃ መሣሪያ
14. ዛክ፡ በከፋ ክፍለ ሀገር የሚገኝ የሙዚቃ መሣሪያ
15. ሸመቶ፡ በከፋ ክፍለ ሀገር የሚገኝ የሙዚቃ መሣሪያ
16. ፋንፋ፡ በከፋ ክፍለ ሀገርና በገሙጐፋ /ኮንሶ/ የሚገኝ የመዚቃ መሣሪያ ነው፡፡
17. አዋዛ፡ በወለጋ ክፍለ ሀገር በአሶሰ አካባቢ የሚገኝ የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡

## የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

1. ከበሮ፡ ለዘፈን ማድመቂያና ለሠርግ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ዝማሬ ቀሳውስት በሽብሽባ ጊዜ የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፡፡
2. አታሞ፡ ለሙዚቃና ለጭፈራ የሚያገለግል መሣሪያ
3. ነጋሪት፡ በሰልፍ ጊዜ የሚጐሰም የሙዚቃ መሣሪያ ነው
4. መቋሚያ፡ ለመንፈሳዊ ዝማሬ ከከበሮው ስልት ጋር በተዛመደ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ቀሳውስት የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፡፡
5. ፀናፅል፡ ለመንፈሳዊ ዝማሬ ቀሳውስት የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፡፡
6. ቅል፡ ቅል በውስጡ ጠጠሮች ወይም ፍሬዎች ተጨምረውበት ለዘፈን ማድመቂያ ያገለግላል፡፡
7. ቻንቻ፡ በገሙጐፋ ክ/ሀገር በጭፈራ ጊዜው በወገብ ላይ የሚታሠር አዳማቂ መሣሪያ ነው፡፡
8. ካመባ፡ ከሸክላ የተሠራ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኝ የምት መሣሪያ ነው፡፡

9. ቃጭል፡ አብዛኛውን ጊዜ ለመንፈሳዊ ዜማ የሚያገለግል መሣሪያ ነው።

10. ቶሞ፡ በጋምቤላ ብሔረሰብ ውስጥ እውቅና ተወዳጅ የሆነ የሙዚቃ መሣሪያ ነው። በተጨማሪም በኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛንያ፣ ናይጀሪያ ፣ ሱዳንና ዛየርም በዚህ መሣሪያ እንደሚጠቀሙ ታውቋል።

11. ጋሬ፡ በጋምቤላ ብሔረሰብ ውስጥ በእግር ላይ ታስሮ ጭፈራን የሚያደምቅ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

12. የግመል ቃጭል፡ ይህ መሣሪያ በተለይ ከእንጨት የሚሠራ ሆኖ ሙዚቃን ለማጀብ የሚጠቅም የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

## የቃላት መውጫ


ሀ

ሀይሉ ዲሳሳ፣18

ለ

ለማ ገ/ሕይወት፣ 26

መ

መልካሙ ተበጀ፣ 13

መሐመድ አህመድ፣ 21

መርዓዊ ስጦታው፣ 24

መርዓዊ ዮሐንስ፣ 16

መስፍን ሃይሌ ፣ 11

ሙላቱ አስታጥቄ፣ 30

ሙሉቀን መለሰ፣ 25

ምኒልክ ወስናቸው፣ 29

ነ

ነዋይ ደበበ፣ 14

አ

አሉላ ከበደ፣ 27

አሰፋ አባተ፣ 15

አበበ ተሰማ፣ 14

አባይ በለጠ፣ 29

አያሌው መስፍን ፣ 9

እሳቱ ተሰማ፣ 7

እዮኤል ዮሐንስ፣ 10

በ

በሻህ ተክለማርያም፣ 19

ባህታ ገ/ሕይወት፣ 8

በኃይሉ እሸቴ፣ 26

ተ

ተሰማ እሸቴ፣ 4

ተዘራ ኃ/ሚካኤል፣ 7

ተፈራ አቡነወልድ፣ 22

ተፈራ ካሳ፣ 23

ታምራት ሞላ፣ 20

ታጠቅ ገ/ወልድ፣ 23

ከ

ኪሮስ አለማየሁ፣ 28

ዐ

ዓለማየሁ እሸቴ፣ 28

ገ

ገላን ተሰማ፣ 22

ጌታመሳይ አበበ፣ 12

ጌታቸው መኩሪያ፣ 25

ግርማ በየነ ፣ 10

ግርማ ነጋሽ ፣ 6

ጠ

ጥላሁን ገሠሠ፣ 5

ፀ

ፀሐዬ ዮሐንስ፣ 20

ፅጌ ማርያም ገብሩ ደስታ፣ 17

ፈ

ፍሬው ሀይሉ፣ 15